## ጠቃሚ ምክር ለተጠቃሚዎች

# የጽዳት ዝርዝር ምሳሌ

ተከራይ በማንኛውም ጊዜ የጽዳት ዝርዝር መኖሩን ከአከራይ ማርጋገጥ ይገባዋል። አከራይ የጽዳት ዝርዝር ካላቀረበ ተከራይ ቤቱን ከመልቀቁ በፊት የሚከተለውን ዝርዝር እንዲጠቀሙ **ይመከራል**

☐ የማቀዝቀዣ ውስጥ፣ ውጪ፣ ሁዋላ እና ስር ማጽዳት እና የበረዶ ቤቱን ማጽዳትና የተጋገረ በረዶን ማስወገድ

☐ የማቀዝቀዣው ኀይል ጠፍቶ ከሆነ በሩን ክፍት መተው

☐ የምድጃ ውስጥ፣ ውጪ፣ ሁዋላ እና ስር ማጽዳት እና ማንደጃውን ማጽዳት

☐ የቁምሳጥኖችን ውስጥና ውጪ ማጠብ

☐ የሁሉንም መስኮቶች፣ ክሎዜቶችና ፓቲዮ በሮችን ውስጥና ውጪ ማጽዳት

☐ ግድግዳዎችንና ውለሎችን ማጽዳት

☐ የመጋረጃ ዘንጎችን እና የመስኮት መከለያዎችን አቡዋራ ማጽዳት ውይም የርስዎን በአከራዩ መቀየር

☐ ንፋስ መስጫዎችንና ንፋስ ማስወጫዎችን ማጠብ ወይም አቡዋራ ማጽዳት፣ የተቃጠሉ አምፑሎችን መቀየር

☐ የጭስ ጠቁአሚው እንደሚሰራ ማረጋገጥ፤ እንደአስፈላጊነቱ መቀየር

☐ የመታጠቢያ ቤት ገንዳ፣ጡብ፣የእጅ መታጠቢያ፣ቫኒቲ፣ መስታወት፣የመድሃኒት ማስቀመጫ፣ቁምሳጥን፣መጸዳጃን ጨምሮ ከዳር እስከ ዳር ማጽዳት

☐ ካስፈለገ ምንጣፍን ቫኪዩም ማድረግና ማጽዳት

# የማገናዘቢያ ዝርዝር ለተከራዮች

## የሚከራየው ቤት

☐ እንደ ብስኪሌት እና ሻንጣ የመሳሰሉ ትርፍ እቃዎችን ማስቀመጫ ቦታ አለ? ቦታውን መጠቅም የሚችል ማነው?

☐ በቅርብ ያለው የአወቶቡስ ማቆሚያ የት ነው?

☐ ቤቱ ዘወትር ለሚፈለጉ አገልግሎቶቸ ቅርብ ነው?( ገበያ፣ባንክ፣ የሰውነት ማጎልምሻ)

☐ ቤቱ ንፁህ ነው? በረዶ የሚጠርገው እና ሳር የሚያጭደው ማነው? መሳሪያዎቹን(አካፋ፤ የሳር ማጨጃ) ይሚያቀርበውስ ማነው?

☐ መኪና የት ማቆም ይቻላል? ውጪውና የመኪና ማቆሚያው በቂ ብርሃን አለው?

☐ ቤቱ በምሽት ለመተኛት ወይም ለማጥናት ምን ያህል ፀጥታ ወይም ጫጫታ አለው?

☐ የልብስ ማጠቢያ ማሽን አለ? የመጠቀሚያ የጊዜ መርሃግብር አለው? ክፍያ አለው? በቅርብ ያለው በሳንቲም የሚሰራ የሕዝብ ልብስ ማጠቢያ ማሽን የት ነው?

☐ ሕንፃው የኢንተርኔት አገልግሎት አለው ወይም አገልግሎቱን ማስገባት ይቻላል?

## ገንዘብ

☐ ኪራዩ ስንት ነው?

☐ እስከ ኪራዩ ጊዜ ማብቂያ ድረስ በአከራዩ የሚያዝ ተቀማጭ ገንዘብ ያስፈልጋል?ምን ያህል?

☐ ኪራዩ የሙቀት፣ውሃ፣የመብራት፣ኬብል፣ ወይም ኢንተርኔት አገልግሎትን ያጠቃልላል?

☐ አገልግሎቶችን ለማስቀጠል ተጨማሪ ክፍያ አለው? (ለተጨማሪ መረጃ የሚለውን ህትመት በዚህ ድህር-ገፅ ላይ ይምልከቱ፡ www.servicealberta.ca/644.cfm/#tipsheets)

☐ መኪና ማቆሚያ ቦታ ተጨማሪ ክፍያ አለው? ስንት ነው?

☐ ለጥገና የሚከፍለው ማነው -ለትላልቅ እና ጥቃቅን?

## ከደባል ጋር አለመግባባቶችን ማስወገድ

☐ የኪራይ ስምምነቱን ማነው የሚፈርመው? የሁሉም አካላት ስም በኪራይ ስምምነቱ ላይ ቢጠቀስ ጥሩ ነው።

☐ አንዱ ግለሰብ የኪራዩ ጊዜ ከማለቁ በፊት ቤቱን መልቀቅ ከፈለገ ምን ይደረጋል?

☐ ወጪዎች እንዴት ይካፈላሉ? ሒሳቦች እንዴት ይከፈላሉ?

☐ ችግሮች እንዴት መፍትሄ ያገኛሉ?

## ጥያቄዎች እና ለግንዛቤ

☐ የኪራይ ስምምነቱ ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ከወር እስከ ወር?

☐ ኪራይ መቼና የት ይከፈላል? ከዘገየ ምን ይሆናል? ለማንኛውም ክፍያ ደረሰኝ ቢኖር ይመረጣል።

☐ ችግር ካለ ለማን ያሳውቃሉ?

☐ የተከራይ መድህን ለመግባት አመቻችተዋል?

☐ ሌሎች ተከራዎቸና ደባሎች ጥሩ ናቸው?

☐ ለማዳ እንስሳ ይፈቀዳል?ተቀማጭ ገንዘብ ያስፈልጋል?

☐ ሲጋራ ማጨስ ይፈቀዳል?

☐ እንግዶች ለምን ያህል ጊዜ መቆየት ይችላሉ?

☐ ቤቱን ማስጌጥ እችላለው?ግድግዳው ላይ ሚስማርና ስፒል ስለመብሳት ያለው ደንብ ምንድነው?

☐ ከቤቱ በመልቀቂያ ጊዜ ማስታወቂያ መቼና የት ነው የሚሰጠው?

☐ የቤቱ ምርመራ ሪፖርት የሚያልቀው መቼ ነው?

☐ የኪራይ ስምምነት፤የምርመራ ውጤት፤ደረሰኝን ጨምሮ ሁሉንም የኪራይ ሰነዶች ቅጂ ማስቀመጥ

ሰርቪስ አልበርታ